

# የሲዳማ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ

## የ2001 በጀት ዓመት የግማሽ ዓመት

## የእቅድ ክንውን

## ሪፖርት

ታህሳስ 30, 2001

ሀዋሳ

# መግቢያ

- ፈጣን ልማትንና መልካም አስተዳደርን ዕውን ለማድረግ የአስፈፃሚንና የፈፃሚዉን አካላት አቅም መገንባት አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን መምሪያችን በተዋረድ የሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶችን እና በጎን የሚገኙ የዞን መምሪያዎችን/ጽ/ቤቶችን በመደገፍና በመከታተል በሪፎርም ስራ የደረሱበትን የክንውን ደረጃ በመለየት በግብረ-መልስ የታገዘ ሥርዓት ዘርግቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

- ከዚሁ ጋር ተያይዞ በበጀት ዓመት ዕቅድ መጀመሪያ ላይ ሴክቶርያል የሆነ የዕቅድ አፈፃፀም ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ፣ ከወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች፣ ከዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ ከሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶችና ፍትህ ተቋማት ጋር በመፈራረም ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የተገባ ሲሆን እስከ አሁን ያሉ በጎ ጅምሮች ወደ ስኬት ሊያደርሱ የሚችሉ ዉጤቶች እየተመዘገቡ ያሉበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን፡፡

- በተለይ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጡን በመጠንና በጥራት ለማሻሻል ከቀየሳቸው እስትራቴጂዎች መካከል መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ /ቢ.ፒ.አር/ መተግበር አንዱ ሲሆን በዚሁም አሰራር የስራ ሂደት የተጠናባቸው መ/ቤቶች ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት የሚስችላቸውን የሰራተኞች ድልድል ስራ በማጠናቀቅ ወደ ስልጠና እየተሰማሩ ይገኛሉ፡፡

## ቁልፍ ዉጤት

- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር፣ ልማትን ለማፋጠን፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ያለንን ዉስን ሀብት በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል ቅንጅታዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም መፍጠር፤

# የታቀዱ ቁልፍ ዝርዝር ዉጤቶች

- በሰለጠነ የሰው ኃይል በአማካይ ከ70% ወደ 90% የደረሱ ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች
- በዞኑ የሰው ሁኔታ ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት
- በሰው ሀብት ልማት ዕቅድ መሠረት በመደበኛና በርቀት ት/ት የረዥም ጊዜ ስልጠና እንዲሳተፉ ዕድል የተሰጣቸው የዞን መምሪያና የወረዳ/ከተማ መ/ቤቶች ሠራተኞች
- በሲ/ሰ/ማ/ፕ እና በወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ የሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እና ለ528 የገጠር ቀበሌ ስራ አስኪያጆች የተሰጠ አጭር ጊዜ ስልጠና
- በቪድዮ ኮንፍረንሲንግ ተጠቅመው ስልጠና የሰጡና ችሎት የማስቻል ሥራ የሠሩ 2 የወረዳ አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች

- በዘመናዊ የመረጃ መረብ /LAN/ የተገናኙ 4/አራት/ የዞን መምሪያዎችና የ6/ስድስት/ የወረዳ መ/ቤቶች፤
- በሰርዓተ ጾታና ኤች.አይ.ቪ ኤድስ Internal Mainstreaming የተደረገባቸውና በሴቶች ላይ በተለያየ ሁኔታ ቫይረሱ እያደረሰ ባለው አደጋና ስጋት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጣቸው የ21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች፤
- በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተጣርቶ 100% ፈጣን ምላሽ የተሰጣቸው 21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የቅጥር፣ ምደባ ዝውውርና የደረጃ እድገት ጥያቄዎች

## የተፈፀሙ ቁልፍ ዉጤቶች

## የተፈጸሙ ዝርዝር ቁልፍ ዉጤቶች

## 1. በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

### ሀ. በአገልግሎት አሰጣጥ ንዑስ ፕሮግራም

- ለተገልጋይ የሚሰጡ አገልግሎቶች መጠንና ጥራት ለማሻሻል መንግስት ካስቀመጠዉ አቅጣጫ አንጻር በአዲሱ የስራ ሂደት ለዉጥ (BPR) ሙሉ ትግበራ ላይ በተዘጋጁ የስልጠና ሰነዶች ላይ ለ50 የጽ/ቤት ኃላፊዎች ፣ ምክትል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- መ/ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት ለተገልጋይ ግልፅ በማድረግ ቅድመ ሁኔታዎች ድህረ-ሁኔታዎችን በማሳወቅ ረገድ የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡

- የሴ/መ/ቤቶችን አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ለመከታተልና ለመደገፍ በቼክ ሊስት የታገዘ ክትትል እየተደረገ መ/ቤቶች በአንፃራዊነት በከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ተከፋፍለዋል፡፡
  - ለምሳሌ፡- ቦሪቻ፣ ጎርቼ፣ ዳሌ፣ አለታ ወንዶ፣ ማልጋ፣ ዳራ፣ ሸበዲኖ ወዘተ.....

## ለ. በሥነ ምግባር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- ለልማትና ለመልካም አስተዳዳር መሰረት የሆነውን ተቋማዊና ማህበራዊ ሥነ ምግባር እውን ለማድረግ ለተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - በአለታ ወንዶ ለ209 ወንዶችና 196 ሴቶች ከተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች ለተዉጣጡ ሰዎች የ5 ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## ሐ. በወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- ዉስን በጀትን በፍትሃዊነትና በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችል ስርዓትን ከመዘርጋት አንጻር በመምሪያችን የተጀመረው በጎ ጅምር፤
  - ለምሳሌ፡- ለየቡድኑ የተደረገ የበጀት ክፍፍል አሠራር ተጠናክሮ በተመሳሳይ መልኩ ወደ ወረዳ ጽ/ቤቶች ለማስፋፋት አቅጣጫ ተይዟል፡፡
- በዞንና በወረዳዎች የንብረት ግዥ በአመት ዉስጥ 2 ዙር እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- ነዳጅ አጠቃቀም በጌጅ ልኬት እንዲሆን በመደረጉ እንደበጎ ጅምር የምናየው ይሆናል፡፡

## መ. በሰው ኃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- የመንግስት ተቋማትን በሰለጠነ የሰው ኃይል ለሟሟላት ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተመርቀው የወጡ ወንድ 190 እና ሴት 22 በድምሩ 212 ባለሙያዎች በሙያ ዘርፋቸው በተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ተመድበዋል፡፡
- የሲቪል ሰርቫንቱን አቅም ለማጎልበት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በተለያዩ የትምህርት መስኮች በመደበኛው ፕሮግራም የሚሳተፉ ዕጩዎች ተመልምለዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በ2002 የት/ዘመን ወደ ኮሌጁ እንዲገቡ የተመለመሉ፤
  - በልማት ሥራ አመራር ወንድ 8፣ ሴ 1፣ በድምሩ 9 ዕጩዎች
  - በከተማ ፕላን ወንድ 4፣ ሴ 1፣ በድምሩ 5 "
  - በፐብሊክ ፋ/ማኔጅመንት ወንድ 7፣ ሴ 1፣ በድምሩ 8 "
  - በከተማ ምህንድስና ወንድ 4፣ ሴ 1፣ በድምሩ 5 "

በአጠቃላይ 27 ዕጩዎች ዝርዝራቸው ተላልፎአል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም በDevelopmental Economics የት/ዘርፍ አንድ ወንድና አንድ ሴት በድምሩ ሁለት ሰዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተልከዋል፡፡
- እንዲሁም በ2001 የት/ዘመን በሁለተኛ ሴሚስተር ወደ ኮሌጅ እንዲገቡ በFedaralism and Local Government Studies የት/ዘርፍ 4 ዕጩዎች መግቢያ ፈተና ተፈትነው ዉጤት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

- በአዲሱ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ/BPR/ በተደረገው የሠራተኞች ድልድል በአቅም ግንባታ ሴክተር መስሪርቱን አሟልተው በዋና የሥራ ሂደትና በደጋፊ የስራ ሂደት ምደባ ያገኙ ሠራተኞች 117 ሲሆኑ ይህም በመቶ 54% ይሆናል፡፡
- ከዚህ ጋር ተያይዞ ደንብን ያልተከተለ ድልድል በተካሄደባቸው መ/ቤቶች አልፎ አልፎ ዉዝግብ እየተፈጠረ ቢሆንም ከዞን አቅ/ግ/መምሪያ ማብራሪያ እየተሰጣቸው አልፎ አልፎ መሻሻሎች እየታዩ ይገኛሉ፡፡ በተለይ በአንዳንድ ወረዳዎች፤
  - <u>ለምሳሌ</u>፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ በምልመላና በምደባ ዙሪያ ከ50 ወንድና ከ11 ሴት በድምሩ 61 ሰዎች ጋር ዉይይት ተደርጓል፡፡

- በአቅም ግንባታ ሴክተር የቅጥርና እና መመሪያን በማይቃረን መልኩ እስከ ወረዳ ባሉ ጽ/ቤቶች የ25 ሰራተኞች ቅጥር ተከናዉኗል፡፡
  - ለምሳሌ፡- ጎርቼ፣ ወንዶ ገነት፣ ቡርሳ፣ ሎካ አባያ፣ ዳራ፣ ቦና ዙሪያ ወዘተ.....
- በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት ወይም የተለያዩ ህጋዊ ጥቅማ ጥቅሞች ከማግኘት አንፃር ለቀረቡ አቤቱታዎች በወቅቱ ምላሽ በመስጠቱ ተገቢ ማሻሻያ የተደረገበት ተጨባጭ ሁኔታ ታይቷል፡፡
  - ለምሳሌ፡- ከጩኮ ወረዳ ለቀረበ የመምህራን የደምወዝ ማስተካከያ አቤቱታ ለ111 ወንድ እና ለ 42 ሴት በድምሩ ለ159 መምህራን ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ በህገ ወጥነታቸው የታገዱ ቅጥሮችን በተመለከተ በበንሳ ወረዳ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የተከሰተውን “ ህገ-ወጥ ” የተባለውን 4 ቅጥርና 1 የደረጃ እድገት አፈጻጸሞች ለማጣራት ከመምሪያችን አጣሪ ቡድን የተላከ ሲሆን ማስተካከያ የሚደረግበት አግባብ እንዲመቻችና የወጣውን የመንግስት ወጪ ወደ መንግስት ካዝና እንዲመለስ ለሚመለከተው ክፍል ደብዳቤ ተጽፏል፡፡
- በሎካ አባያ ወረዳ የተፈጸመው 1 ህገ ወጥ የደረጃ እድገት እንዲታገድ ተደርጓል፡፡

- የዞኑን የመንግስት ሠራተኞች ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት በተመለከተ አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ ጠብቀው ባይመጡም በተደረገው ያላሰለሰ ጥረት ለጥናቱ ግብአትነት የሚፈለጉ መረጃዎች የደረሱን ቢሆንም ትንተናው በተያዘለት የጊዜ ገደብ ሊጠናቀቅ አልቻለም፡፡
- ለዚህም በምክንያትነት ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም አዲሱ መሠረታዊ የስራ ሂደት ለዉጥ ትግበራ /BPR/ ዝግጅት በዋናነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡
- ወቅታዊ የሰው ኃይል መረጃ ከሁሉም የዞን መምሪያዎችና ከአብዛኛዎቹ ወረዳዎች የተሰበሰበ ሲሆን ከጎርቼ እና ከአሮሬሳ ወረዳዎች ብቻ ሊደርሰን አልቻለም፡፡

## ሥ. በበላይ ሥራ አመራር ስርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- ልማትንና መልካም አስተዳደርን እውን ለማድርግ የበላይ አመራሩ ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑና ለውጥን ለመምራት የመሪው ተነሳሽነት ወሳኝ ስለሆነ በተለይ በአዲሱ መሠረታዊ የአሰራር ለውጥ /BPR/ ዙሪያ በወረዳዎቹ አቅ/ግ/ጽ/ቤት በኩል ለአመራሩ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
  - ለምሳሌ፡- አለታ ወንዶ ወረዳ፣ በአርቤጎና ወረዳ ወዘተ....

## 2. በፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

- የህረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ ለመመለስ የፍትህ ተቋማት አቅም ማጠናከር ወሳኝ እንደመሆኑ ሁሉም አካላት በቅንጅት ለአንድ አላማ የሚሠሩበት አቅጣጫ እየጎላ መጥቷል፡፡ በተለይ ሚሊሽያ፣ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ህግና ፍርድ ቤት እርስ በርሳቸው እየተናበቡ የሚሰሩበትን አሰራር ከነጉድለቱም ቢሆን የተሻለ እምርታ እየታየበት ይገኛል፡፡

## ሀ. በምክር ቤት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- በመልካም አስተዳደርና በልማት ዘርፍ የተሰሩና የሚሰሩ ስራዎች በምክር ቤቱ የበላይ አመራር ወቅታዊ ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፡፡ በተለይ በቀበሌ ደረጃ የእቅድ ዝግጅትና ክንውን ደረጃ በሸንጎ እየተገመገመ ሲሆን በጎ ጅምር ይታይበታል፡፡

- የወረዳና የዞን ቋሚ ኮሚቴዎችም የየሴክተሮቹን እቅድ ክንውን በመገምገም አቅጣጫ በማሳየትና ግብረ-መልስ በመስጠት በጎ ጅምሮች እየታዩ ቢሆኑም የበለጠ መስፋፋትና መቀጠል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

## ለ. በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንኡስ ፕሮግራም

- ተቋማቱ የዉሳኔ አሰጣጡን ሂደት የተሻለ ከማድረግ ባሻገር የኅብረተሰቡን በራስ የመተማመን መንፈስ ለማጠናከር በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በአንዳንድ ወረዳዎች በችሎት የሚመደቡ ዳኞች ራሳቸውን በማስተዋወቅና ለባለጉዳዮቹም ሰላምታ በመስጠት፣ ዉጥረትን የማርገብ ልምድ እያዳበሩ ያሉበት ደረጃ ላይ እንገኛለን፡፡



- ባለጉዳይን እስከቦታው ድረስ ሄዶ ከማገልገል አንፃር ፍ/ቤቶች ተዘዋዋሪ ችሎት የማስቻል ስራ በማጠናከር ላይ ይገኛሉ፡፡
  - ለምሳሌ፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ በገርቢቾ ቀበሌና በጎርዳማ ቀበሌ

☆ በተጨማሪም በተቋሙ ዉስጥ አገልግሎት ሰጪ አካላት ራሳቸውን ከተገልጋይ የሚለዩበትን የደንብ ልብስ በመጠቀም ለተገልጋይ የመረጃ ምንጭ በመሆን እያገለገሉ ናቸው፡፡ በተለይ በሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና በሌሎችም ዉስን የወረዳ ጽ/ቤቶች....





## ሐ. በዐቃቤ ህግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- ዐቃቤ ህግ ከፖሊስ የሚቀርቡለትን መረጃዎች እዉነተኛነት ለማጣራት በቅርበት እየሰራ ያለ ሲሆን ህ/ሰቡ መብትና ግዴታውን አውቆ ወንጀልን እንዲከላከልና ራሱን ከወንጀል ነፃ እንዲያደርግ የንቃተ ህግ ትምህርት አልፎ አልፎ እየተሰጠ ቢሆንም ብዙ መሰራት ይጠበቅበታል፡፡
- ከፍ/ቤት ጋር በመቀናጀት ተዘዋዋሪ ችሎት የማስቻል ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይህም በጎ ጅምር ሲሆን በቀጣይ በሌሎች ቦታዎችም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## መ. በፖሊስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- ፖሊስ ወንጀልን ለመከላከልና ለማጋለጥ ከኅ/ሰቡ ጋር በመቀናጀት እየሠራ ቢሆንም የሰው ኃይል ስርጭቱ ወጣ ገባነት ይታይበታል፡፡

- ይህ በእንዲህ እንዳለ በአብዛኞቹ ወረዳዎች ንዑስ ፖሊስ ጣቢያዎች በመቋቋማቸውና ኅ/ሰቡም በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር የግንዛቤ ማስጨበጫ ዉይይቶች እየተካሄዱ በመሆናቸው የወንጀል ቁጥር በመቀነስ ላይ ይገኛል፡፡

- ለምሳሌ፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ በተቋቋሙ 5 የፖሊስ ጣቢያዎች አንድ አንድ መደበኛ የፖሊስ ኃይል የተመደበ ሲሆን ህ/ሰቡን የማስተባበር የማንቃት ስራ በመሰራቱ ወንጀል እንዲቀንስ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

- በሌሎች ወረዳዎችም፡- በአርቤጎና፣ ዳሌ፣ በዳራ፣ በአለታ ጩኮ፣ በሸበዲኖ ወዘተ..... ወረዳዎች/ከተሞች ንዑስ ፖሊስ ጣቢያዎች ተቋቁመዋል፡፡

## ሠ. በሚሊሽያ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

- የሚሊሽያ አካላት ከመደበኛ ተግባራቸው ሳይለዩ ከህ/ሰቡ ጋር ጎን ለጎን በመሆን ወንጀል የሚከሰትባቸውን ቦታዎች አስቀድሞ በማጥናት መረጃ እንዲያሰራጩና የሚከሰቱ ወንጀሎችንም ወደ ህግ ፊት ለማቅረብ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ግንዛቤ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

## 3. በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ

- የወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶችንና የሌሎች ሴ/መ/ቤቶችን የሥራ ተነሳሽነት መንፈስ ለማነሳሳት በእቅድ ክንዉናቸው መሰረት ደረጃ የተሰጣቸውና ማበረታቻ የተደረገላቸው ሲሆን አፈፃፀማቸውን በብዙሃን መገናኛ እንዲተላለፍ ተደርጎአል፡፡
- አብዛኛዎቹ ሴ/መ/ቤቶች በየሴክተራቸው የክንውን ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን በቀጣዩም አሠራሩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የአፈፃፀም ማኑዋል ለየመምሪያዎቹና በተዋረድም ለየወረዳዎቹ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡

- አብዛኞቹ የገጠር ቀበሌያት የየራሳቸው ጽ/ቤት ያሏቸው ሲሆን በአንዳንድ ቀበሌያት የጽ/ቤታቸውን ራዕይ፣ ተልእኮና እሴት በማዘጋጀት አርአያ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአስተያየት መስጫ ሳጥንም አዘጋጅተዋል፡፡

  - ለአብነት ያህል፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ ሻኢቻ ቀበሌ







ማስታወቂያ
ጉዳዩ፡ የቀበሌውን የሥራ ሰዓት
እና ቀን ለሕዝብ ማሳወቅ ነው
1
የሥራ አስኪያጅ
ቢሮ



- በሌላ በኩል ደግሞ በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ዙሪያ የማጠናከሪያ ስልጠና ከመሰጠቱም ጎን ለጎን በምርጥ አርአያነታቸው ሞዴል ቀበሌዎች፣ ሞዴል የቀበሌ አስተዳዳሪዎች፣ ሞዴል የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ ሞዴል የግብርና ጽ/ቤት ሰራተኞች እና ሞዴል ግለሰቦች የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡

  - ለምሳሌ፡- በአርቤጎና ወረዳ እና እንዲሁም በአለታ ወንዶ ወረዳ ለ135 አርሶ አደሮችና ለ27 ስራ አስኪያጆች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የቀበሌ ስራ አስኪያጆች በቀበሌ ዉስጥ የሚሰሩ ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችንና የልማት ሰራተኞች የስራ ሰዓት በመከታተል በወሩ መጨረሻ ክሊራንስ እየተሰጣቸው ደመወዝ የሚያገኙበት አሠራር እየተጠናከረ ይገኛል፡፡
  - <u>ለምሳሌ</u>፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ በገጠር የሚሠሩ የመንግስት ሠራተኞች በአራት ካላስተር ደመወዝ እየተከፈላቸው ያለ ሲሆን ከፋዮች የመለያ ገዋንና ባጅ እየተጠቀሙ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የይርጋአለም ከተማ በየት/ቤቱና በየጽ/ቤቱ ይህንን አሰራር ተግባራዊ እያደረገ በጎ ጅምር እየታየ ይገኛል፡፡

- የወረዳውንና የጽ/ቤቱን ምርጥ ተሞክሮ እና እንዲሁም የግለሰብ ተሞክሮዎችን ከማስፋፋት አንፃር 11 ወረዳዎች፡- አለታ ወንዶ፣ ዳራ፣ ሀዋሳ ዙሪያ፣ ቦሪቻ፣ ሸበዲኖ፣ ይ/ዓለም፣ ቡርሳ፣ አለታ ጩኮ፣ አሮሬሳ፣ ቦና ዙሪያ፣ አለታ ወንዶ ከተማ የሴክተር፣ የቀበሌ፣ የመንደርና የግለሰብ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምረው ሪፖርት አስተላልፈዋል፡፡

- ከዚህ ጋር ተያይዞ መልካም ተሞክሮዎችን ለማስተዋወቅ በብዙሃን መገናኛ የአየር ሽፋን ተሰጥቷል፡፡

  - ለምሳሌ፡- በአለታ ወንዶ ወረዳ የተሰራ ሥራ፣ በወንሾ የተሰጡ ሥልጠናዎች፣ በሸበዲኖ ወረዳ በአንድ አርሶ አደር የተሰራ የመስኖ ሥራ ዉጤታማነት የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን ተሰጥተቷቸዋል፡፡







- የየወረዳው ማህበረሰብ የመልካም አስተዳደርና የልማት ዕቅዶችን በመሥራት ለተሻለ ዉጤት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡
- በተለይ በወልና በግል የሚሠሩ ስራዎችን በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርናና ገጠር ልማት፣ በአቅም ግንባታ ዘርፍ ሥር ነቀል የሆነ ዕቅድ በማቀድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ሞዴል ቀበሌን፣ መንደርንና ግለሰብን በፓኬጁ መስፈርት መሰረት የመምረጡና የመፍጠሩ ሥራ ጉድለት ቢኖርበትም በአለታ ወንዶ ወረዳ፣ አርቤጎና፣ ዳራ፣ ሸበዲኖ፣ ሀዋሳ ዙሪያ….. ወዘተ ወረዳዎች የተሻለ መልክ የያዘ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡









## ሀ/ በመልካም አስተዳደር መርሆዎች ዙሪያ

- በስምንቱ መርሆዎች ዙሪያ በህ/ሰቡ ዘንድ ምን እንደተከናወነ በዝርዝር ለማወቅና ብሎም ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከወረዳ እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

# በተሳትፏዊነት

- በሁሉም ወረዳዎች በልማትና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ሁሉ በህ/ሰቡ ተሳትፎ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡
  - ለምሳሌ፡- ህ/ሰቡ በየቀጠና በልማት ቡድን ተደራጅተው የጋራ ምንጮችን በማጎልበት የጋራ መጠቀሚያ መፀዳጃ ቤቶችን፣ ት/ቤቶችን በመገንባት፣ ነባር ት/ቤቶችን በማስፋፋት፣ በድልድይ ግንባታ፣ ቀበሌን ከቀበሌ፣ መንደርን ከመንደር የሚያገናኙ ጥርጊያ መንገዶችን በመስራት የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የመምህራን ማደሪያ በመገንባት ወዘተ… ስራዎች ተሳትፈዋል፡፡

## በጋራ መግባባት

- በሁሉም ወረዳዎች በተለይ በወል የሚሠሩ የልማት ሥራዎችን በጋራ መድረክ ተወያይተው በማጽደቅ በብዙሃን ስምምነት መሠረት በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

## ቶሎ ምላሽ መስጠት

- የህብረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ ለመመለስና የአገልግሎት ፍላጎት ለማርካት እየተሰራ ያለው ስራ በአጠቃላይ በጎ ገጽታ የሚንጸባረቅበት ቢሆንም በቀጣይነት በተጠናከረ መልኩ ብዙ መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡
    - ለምሳሌ፡- በአንዳንድ የወረዳ ቀበሌዎች ባለጉዳይ ከቀበሌው ስራ አስኪያጅ ጋር በመገናኘት ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸው፣ በቀበሌው አመራር ዉሳኔ እየተሰጣቸው የሚገለገሉበት አሠራር ተጀምሯል፡፡ በቀጣይም መጠናከር የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

## ግልጸኝነትና ተጠያቂነት

- የየቀበሌው የዕቅድ አፈፃፀም፣ የበጀት አሰባሰብና አጠቃቀም ሪፖርቶች በምክር ቤት አማካይነት እየቀረቡ በመሆናቸው የግልጸኝነትና የተጠያቂነት ሥርዓት በማዳበር ላይ ይገኛል፡፡
- በጀትን ይፋ በማድረግ በኩል የተወሰኑ ወረዳዎችና የዞን መምሪያዎች የአመት በጀታቸውን ለተገልጋይ ግልጽ በሆነ ቦታ ለጥፈዋል፡፡

# ፍትሃዊነትና የህግ የበላይነት

- የህብረተሰቡ የፍትህ ጥያቄ ከምን ጊዜውም በተለየ ሁኔታ ጫና እየተፈጠረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ፍትህ ሰጪ አካላትም ከህግ የበላይነት አንጻር ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

- ህብረተሰቡ የህግ የበላይነትን አውቆ መብቱን እየጠበቀ ግዴታውን እየተወጣ በልማትና በመልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ ተሳትፎው እየጨመረ ነው፡፡ ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በተለያየ ወረዳዎች ተግባራዊ በመሆን ላይ ናቸው፡፡

  - ለምሳሌ፡- አለታ ወንዶ፣ ዳራ፣ አርቤጎና፣ ወንሾ፣ ሀዋሳ ዙሪያ

## ቀልጣፋነትና ዉጤታማነት

- ለተገልጋይ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፈጣንና ዉጤታማ ለማድረግ እየተሰሩ ካሉ ስራዎች መካከል አንዱ ተገልጋይ ማመልከቻ በመጻፍ የአገልግሎት ፍላጎት ጥያቄ እንዳያቀርብ በማድረግ በመሆኑ የተለያዩ ቅጻ ቅጾችና ማመልከቻ ፎርማት ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ መዋል ጀምረዋል፡፡
  - ለምሳሌ፡- አለታ ወንዶ፣ ዳሌ፣ አርቤጎና፣ ወንሾ፣ ሀዋሳ ዙሪያ፣ ማልጋ፣ ጎርቼ ወዘተ…

# በኢኮቴ ማሻሻያ ፕሮግራም

- የወረዳዎችንና የዞን መምሪያዎችን አቅም ለመገንባት ከክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ የተሰጡ 60 ስካነሮችና 10 ኮምፒዉተሮች ለ18 የዞን መምሪያዎችና ለ21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግባታ ጽ/ቤቶች ተከፋፍለዋል፡፡

- የየሴክተሩን ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎት ለማዳበር ፅንሰ-ሀሳባዊና ተግባራዊ ስልጠናዎች የወረዳኔት ባለባቸው ማዕከላት እየተሰጡ ሲሆን በዞን መምሪያ ደረጃ በክልሉ የኢ.ኮ.ቴ ማዕከል 46 ወንድ እና 4 ሴት በድምሩ 50 ተሿሚዎችና ሠራተኞች በመሠረታዊ የኮምፒዉተር ትምህርት፤ በPower Point, Excel እና በኢንተርኔት በአጠቃቀም ላይ ሠልጥነው ተመርቀዋል፡፡

- በተመሳሳይ በአለታ ወንዶ 40 ወንድ እና 14 ሴት በድምሩ 54 ባለሙያዎች የ3 ወር ተከታታይ የኮምፒዉተር ሥልጠና ወስደው ተመርቀዋል፡፡ እንዲሁም በዳራ 76 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ሰልጥነው የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል፡፡

- ሸቦ አልባ ስልኮች የተጠሪነት ጥያቄ እያስነሱ ያሉ ቢሆንም በአቅም ግንባታ ጽ/ቤት በኩል ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ እስካሁን የተሰራጩ ስልኮች ከነጉድለታቸውም ቢሆን ሰፋ ላለ የማህበረሰብ ክፍል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

- **ለአብነት ያህል** :- በአለታ ወንዶ ወረዳ 9 ሽቦ አልባ ስልኮች ለ2000 ወንድ እና ለ250 ሴት በድምሩ ለ2250 ተጠቃሚዎች አገልግሎት እንደሰጡ ታዉቋል፡፡

- መሥሪያ ቤቶች በመረጃ መረብ በማገናኘት በኩል አበረታች ክንዉኖች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

- **ለምሳሌ** :- በአለታ ወንዶ ወረዳ የ3 ወረዳ ቢሮዎች (የሥራ ክፍሎች) በNetwork ተገናኝተዋል፡፡

- በዳሌ ወረዳ የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኮምፒዉተሮች በLAN ተገናኝተዋል፡፡

- እንደዚሁም በሲዳማ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ የተከናወኑ የጥገና፣ ፕሮግራሞችን የመጫንና የኔትወርክ (LAN) ሥራዎች ከምን ጊዜዉም በተሻለ ሁኔታ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህም ተግባር መ/ቤቶችን ከወጪ ያዳነ መሆኑን ከባለሙያዎች ሪፖርት መገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>**ለምሳሌ**</u>:-

- ለሲዳማ ዞን ሴቶች ጉዳይ መምሪያ "Window Operating System Reinstallation"ተሠርቶ ከብር 400.00 ወጪ
- ለሲዳማ ዞን ፋ/ኢ/ል/መ "Formatting and Repairing Corrupted File" ሥራ ተሠርቶ ከ400.00 ብር ወጪ
- ለሲዳማ ዞን ሥ/ከ/ል/መ 4 ኮምፒዉተሮች ላይ የተከሰተውን "operating File System File Missing" ችግሮችን በReinstallation, Formatting እና በRepairing ተስተካክሎ ከብር 1.400 ወጪ

- ለታክስ አስተዳደር በ2 ኮምፒዉተሮች ላይ የ'Formatting' ሥራ በመሠራቱ ከብር 700 ወጪ ያዳነ ሲሆን እንዲሁም
  - ለሲዳማ ዞን ጤና መምሪያ፣
  - ዉሃ ሃብት ጽ/ቤት፣
  - ሎካ አባያ ወረዳ አቅ/ግ/ጽ/ቤት እና አስተዳደር፣
  - ወንሾ አቅም ግንባታ፣
  - በንሳ አቅ/ግ/ጽ/ቤት፣
  - ዳራ አቅ/ግ/ጽ/ቤት፣
  - ዳራ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት
  - ሲ/ዞ/ወ/ስፖርት መምሪያ፣
  - ለሲዳማ ዞን ት/መምሪያ፣
  - ለጎርቼ አቅ/ግ/ጽ/ቤት እና አስተዳደር ጽ/ቤት፣
  - አርቤጎና አቅ/ግ/ጽ/ቤት

የኮምፒዉተር ጥገና ስራ ተሰርቷል::

- በአጠቃላይ የተሠሩ ሥራዎች በገንዘብ ሲተመኑ ከ13,700 ብር በላይ ወጪ ያዳነ ሥራ ተሠርቷል፡፡
- ከዚህ ጋር ተያይዞ በዞን ማዕከል የት/መምሪያና የወጣቶችና ስፖርት መምሪያ በLAN ተገናኝተው የመረጃን ፍሰትና ቅብብሎሽ ፈጣንና ቀልጣፋ ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፡፡

# በሥርዓተ ፆታና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ

- ሁሉም የአቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ለመ/ቤታቸው ሠራተኞች ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አስከፊነትና ጎጂነት ብሎም መከላከያ መንገዶች የግንዛቤ መድረክ ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

- ሁሉም የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ከመደበኛ በጀታቸው ላይ ተጠቂዎችን መደጎሚያ 2% መድበዋል፡፡ ከሠራተኞቻቸው የወር ደመወዝ ላይ 0.5% እንዲዋጣ አድርገዋል፡፡

- "የመንግስት መ/ቤቶችና ሠራተኞች የስራ ቦታዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ" እና የተለያዩ ብሮሸሮች ለሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች ተሰራጭተዋል፡፡

- በሁሉም ሴ/መ/ቤቶች የሚሠሩ ቋሚ የሴት ሠራተኞችን ቁጥር በመለየት በአጠቃላይ 2464 ሴቶች የተገኙ ሲሆን ሴ-ወ ጥምርታው 1:4 መድረሱ ታዉቋል፡፡
- በመ/ቤት ደረጃ Internal Mainstreaming ለማድረግ የሲዳማ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ ከሲዳማ ዞን ጤና መምሪያ ጋር በመተባበር በዓለም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቀን ለሠራተኞች በሙሉ የአንድ ቀን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን ሠራተኞች በጋራ ዉይይት ላይ ተሳትፈዋል፡፡

# ያልተፈጸሙ ቁልፍ ዉጤቶች

- በቪድዮ ኮንፍረንሲንግ ቴክኖሎጂ አማካይነት ሥልጠና መስጠት ችሎት የማስቻል ሥራ አለመሰራቱ፤
- በዞን ደረጃ የተገልጋይ ተኮር አገልግሎት አሰጣጥ ቀን አለመከበሩ፤
- ከወረዳዎች ጋር በኢንተርኔትና በኢ-ሜይል ቴክኖሎጂ አማካይነት መረጃ የመለዋወጥ ሥራ አለመሰራቱ፤

# የታቀዱ አበይት ዉጤቶች

## በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ

- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው 17 የዞን መምሪያዎች/ጽ/ቤቶች፣ የ21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች፣ 114 ሞዴልና 414 ሞዴል ያልሆኑ የገጠር ቀበሌያት፤
- ግብረ-መልስ የተሰጣቸው የተለያዩ መ/ቤቶችና የገጠር ቀበሌያት፤
- የየሩብ ዓመት ዕቅድ ክንውን ሪፖርት በወቅቱ ያስተላለፉ የ21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤
- የሴክተሮችን የየሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም የገመገሙና ደረጃቸውን ያሳወቁ የ21 ወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤

# የታቀዱ ዐበይት ዝርዝር ዉጤቶች

## በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ላይ ድጋፍን ክትትል ማድረግ

- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ላይ ድጋፍና ክትትል የተደረገላቸው ሴ/መ/ቤቶችና ገጠር ቀበሌያት፤
- ግብረ-መልስ የተሰጣቸው መ/ቤቶችና የገጠር ቀበሌያት፤
- የዕቅድ ክንውን ግምገማ የተደረገባቸው ሴ/መ/ቤቶችና ቀበሌያት፤
- በወቅቱ የተላለፈ የእቅድ ክንውን ሪፖርት፤

# የተፈፀሙ ዐበይት ዉጤቶች

- የወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ሴክተር መ/ቤቶችንና የገጠር ቀበሌያትን TOR(ቢጋር) በማዘጋጀት የሪፎርሙን ሥራ በመከታተል የአቅም ዉስንነቶችን የመቅረፍ ሥራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በተለይ በአለታ ወንዶ ወረዳ፣ በአርቤጎና፣ ዳራ፣ በንሳ፣ ሸበዲኖ፣ ወዘተ…..

- በተለይ በሴክተር መ/ቤቶች ደረጃ የአፈፃፀም ግብረ-መልስ አሰጣጥ የተሟላ ባይሆንም በጥቂት ወረዳዎች ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በዞን ማዕከላት ለሚገኙ የተወሰኑ መምሪያዎች የሪፎርም ሥራ አፈፃፀምን የተመለከተ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡፡

- በገጠር ቀበሌያት ደረጃ ጎልቶ ባይታይም በወረዳዎቹ ሴ/መ/ቤቶች የዕቅድ አፈፃፀማቸው በቼክ ሊስት እየታየ ደረጃ ወጥቶላቸዋል፡፡
  - በጭሬ፣ በአለታ ወንዶ፣ በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ፣ የገጠር ቀበሌያት ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን ሴክተር መ/ቤቶችም በ"ከፍተኛ" በ"መካከለኛ" እና በ"ዝቅተኛ" ደረጃ ተለይተዋል፡፡

# ያልተፈፀሙ ዐበይት ዝርዝር ውጤቶች

- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ላይ የታቀደውን ያህል ድጋፍና ክትትል ለማድረግ አለመቻሉ፤
- ጥብቅና መደበኛ፣ ያልቀዘቀዘ ወቅታዊ የአፈፃፀም ግብረ-መልስ አሟልቶ አለመስጠት፤
- የዕቅድ ክንውን ሪፖርት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ አለመተሳለፉ፤

## የእቅድ አፈፃፀም ደረጃ

1. በቁልፍ የትኩረት መስክ 85%
2. በአበይት የትኩረት መስኮች 90%

# በእቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

**ጠንካራ ጎኖች**

- ☆ አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ ማትጊያ ለወረዳ/ከተማ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች መሰጠቱ፤
- ☆ በኢ.ኮ.ቴ ባለሙያዎች በመጠቀም የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ከ13,700 ብር ወጪ ማዳን መቻሉ፤
- ☆ በተገኙ መልካም አጋጣሚዎች/መድረኮች የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን ለህ/ሰቡ ይፋ መደረጉ፤ በተለይ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችንና የልማት ስራዎችን በሲዳማ ሬድዮ ማሰራጨት መቻሉ፤
- ☆ የተሻለ አሠራርና አፈፃፀም ያሳዩ ወረዳዎች ተሞክሮን ሌሎች እንዲቀስሙ መደረጉ፤

- የበላይ አመራሩን የሥራ ተነሳሽነት ዕውን ለማድረግ ስልጠና መስጠቱ፤
- ህገ ወጥ ቅጥሮችንና የደረጃ እድገቶችን ተከታትሎ እንዲታረሙ መደረጉ፤
- በአንዳንድ ወረዳዎች የሞዴል ግለሰብ፣ መንደር እና ቀበሌ አመራረጥ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መመሪያን ብቻ የተከተለ እንዲሆን የማድረግ ጅማሮ መኖሩ፤
- ለየወረዳዎቹ ጽ/ቤቶችና ለየቀበሌዎቹ አንድ አንድ ተጠሪ የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ባለሙያ ተመድቦ የዕለት ተዕለት ክትትልና ድጋፍ መደረጉ፤

## ደካማ ጎኖች

- የተሻሻለው የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በአወቃቀሩ መሠረት ትኩረት ተሰጥቶት ወቅታዊ የአፈፃፀምና የአሰራር አቅጣጫ ቢቀመጥም የተፈለገውን ዉጤት በተቀመጠለት ጊዜ ማምጣት አለመቻሉ፤
- ከወረዳዎች/ከተሞች አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የሚላኩ ሪፖርቶች በወቅቱና በተፈለገው ጥራት አለመላካቸው፤
- የወረዳኔት በሌለባቸው አካባቢዎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በሚገባ መጠቀም አለመቻል፤
- የወረዳኔት ያላቸው የወረዳ/ከተማ ጽ/ቤቶች ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ሪፖርቶችንና መልዕክቶችን በኢ-ሜይል ለመላክ ያላቸው ተነሳሽነት አነስተኛ መሆኑ፤

# በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች

- ለማቴሪያል ግዥና ለስልጠና ሂደቶች የሚጠየቁ ወጪዎች ፍሰት ፈጣን አለመሆን፤
- ሥልጠና ለመስጠትና ኢንተርኔትን ለማስጠቀም በቂ ቁጥር ያላቸው ኮምፒዉተሮች አለመኖር፤
- በተለይ አዳዲስ ወረዳዎች በቂ የቢሮ አደረጃጀት አለመኖር፤
- በቂ ተሽከርካሪ ባለመኖሩ በየጊዜው በአካል ተገኝቶ ክትትልና ድጋፍ በወቅቱ ማድረግ አለመቻሉ፤

# የተወሰዱ መፍትሄዎች

- የወጪዎቹን ፍሰት ፈጣን ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርና አብሮ በመስራት ችግሩ እንዲቀረፍ ተደርጓል፡፡
- ያሉ ኮምፒዉተሮችን በመጠቀም አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ተደርጓል፡፡
- ባሉ ቢሮዎች በመጠቀም አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ተደርጓል፡፡
- የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ባሉባቸው ወረዳዎች የህዝብ ትራንስፖርቴሽን በመጠቀም ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

# ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

- በኢ.ኮ.ቴ የወረዳኔት ባልተዘረጋባቸው ወረዳዎች የዝርጋታ ስራ ለመስራት ከሚመለከተው አካል ጋር ግንኙነት መፍጠር፤
- የህ/ሰቡን የመረጃ ልውውጥ ለማስፋፋት ተጨማሪ ገመድ አልባ ስልኮች የሚሰራጩበትን አቅጣጫ መቀየስ፤
- የፍትህ ስርዓት ማሻሻያው እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
- በBPR የሠራተኞች ድልድል ምደባ ያላገኙ ሠራተኞች ምደባ እንዲያገኙ ወይም አማራጭ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ማድረግ፤

# ማጠቃለያ

- በአጠቃላይ እንደ አገር፣ እንደ ክልልና እንደ ዞን የተነደፈው ራዕይ ከተቀመጠለት ጊዜ አንፃር በተገቢው ፍጥነት እየሄደ ነው ባንልም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአመለካከትና ከአሰራር ጀምሮ መሻሻሎች በመታየት ላይ ናቸው፡፡
- ይህ ልማት የመልካም አስተዳደር ተስፋ አምንታዊ ገጽታው እየጎላ እንዲመጣ የሁሉም አካላት ርብርብ ወሳኝ በመሆኑ ባስመዘገብናቸው ድሎች ሳንደላደል የበለጠ ለመስራት ብንነሳሳ ልማቱንና መልካም አስተዳደርን ዕውን ማድረግ እንችላለን ብለን እናምናለን፡፡


አመሰግናለሁ!